# ደም ተመረመረ

ዘመን ተለወጠ፣
                ቀን ተቀያየረ፣
ለአቻ ጋብቻ፣
                ለጥምረቱ ኑሮ
በአጥንት መመካት መፈረጃ ቀረ፣
በዘመነ ቫይረስ ደም ተመረመረ።

የማነው ልጅ ማለት፣
በዘር ማምለክ በአያት፣
በሀብት መመካት፣
ያኔ ድሮ ቀረ፣
በዘመነ ቫይረስ ደም ተመረመረ።

አጥንቱ የነፃ ልክ እንደ በረዶ፣
በጩማ ያደገ በጠጅ በብርንዶ፣
ማለት ድሮ ቀረ፣
በዘመነ ቫይረስ ደም ተመረመረ።

መጠናናት ቀረ “ከስር መሰረቱ”
ሰው ደሙ ከነፃ ቢቆሸሸ አጥንቱ።



este_dar@yahoo.com

**ማስጠንቀቂያ**

**ትእዛዝ ከሆነ ይሁንና።**
**መገፋትም ከሆነ እሺ።**
**ቁጣም ይሁን ግድ የለም።**
**ስድብም ከሆነ ምንም አይደል።**
**ብልጠቱንም አወን አወን።**
**ተንኮሉንም አሜን አሜን።**
**ረሃቡም የለምድነው ጥማቱም ቢሆን ከርሞብናል፣**
**አይቻል የለምና እስሩም ቢሆን ይቻላል።**
**ግርፋቱ ቢያስከፋም ከንፈር ተመጥጦ ዝም ይባላል።**
**የልጆች ሞት ላይ ግን ዝም የለም፣**
**ሆላ ልብ አርጉ ብለናል።**

este_dar@yahoo.com